# ፖለቲካን ከፕሮፖጋንዳ የማይለዩ.....

ዮናስ 07/03/14

የዚህ ፅሁፍ ትኩረት  ስለፖለቲካ እና ፕሮፖጋንዳ ማስተማር ሳይሆን ቀጣዩን  የ2007 ምርጫን  ምክንያት በማድረግ ከወዲሁ እንደተለመደው አንዳንድ ተቃዋሚዎች አሁንም ከፈረሱ ጋሪውን አስቀድመው በህዝብ ስም ለመነገድ እየሞከሩ ቢሆንም ህዝቡ ግን ከጋሪው ፈረሱን ያስቀደመ አነዳድ ላይ መገኘቱን ማመላከት ነው፡፡

ከምርጫ 97 በኋላ  ከሁለንተናዊ የፖለቲካ ሁኔታ እና ከነበረው ስህተት አብዛኞቹ መማር ያልቻሉና ይልቁንም በዚያው መንፈስ ወደባሰው አዘቅት እያወረዱ መሆኑንም እያስዋልን ነው፡፡ በወቅቱ እንደ ቅፅበታዊ ነጎድጓድ ብልጭ ብሎ ድርግም ያለውና ስሩ እንዴት ሊበጣጠስ እንደቻለ የመረመሩና የተገነዘቡ በአዲስ የሰው ሃይል እንኳ ባይሆን በአዲስ አስተሳሰብ እራሳቸውን ማረማቸውና በዚያው አግባብ ፖለቲካዊ ቁመናቸውንም ማስተካከላቸው አይካድም፡፡ ያም ሆኖ ግን በወቅቱ ለነበረው የመፈረካከስ አደጋ ምክንያት የነበሩትና ዋነኛ መንስኤ የሆኑቱ ወደአዘቅት ከወረወራቸው አደጋና መስመር ሊማሩ ሲገባና ይማሩ ይሆናል ተብሎ ሲጠበቅ ይኸው አድሮ ቃሪያ ሆነው አንዱን አሳልፈው ሁለተኛው የምርጫ ዋዜማ ላይ እየባሰባቸው መሆኑን እየተመለከትን ነው፡፡

ይህ ጉዳይ በዋናነት የሚመለከታቸውና በጉዳዩ የሚገለፁትም በተለይ በምርጫ 97 ወቅት እራሳቸውን እንደአውራ ቆጥረው የስልጣን ሽኩቻውን በፊት አውራሪነት ሲያስፈፅሙ የነበሩት መኢአድና የቅንጅቱ ፍንካች የሆነው አንድነት የተሰኙት ፓርቲዎች ናቸው፡፡ አንድነትን ጨምሮ መኢአድ ግን የሌለበት መድረክ የተሰኘ የፓርቲዎች ጥምረት ቅንጅት ፈጥሮት ያመለጠውን አጋጣሚ ለመጠቀም በምርጫ 2002 ዋዜማ ላይ የተመሰረተና ከምርጫ 97ቱ ቅንጅት ጥንካሬ እና ድክመት ሳይማርና ሳያገናዝብ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤትን ግብ ያደረገ ስልቱን  በፕሮፖጋንዳ አጅሎ ቢመጣም ሳይሳካ እንደቀረ ይታወሳል፡፡

በመድብለ ፓርቲ የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ስር ስለዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ሊወዳደርና ስልጣንን ለመረከብ የሚሻ የትኛውም ፓርቲ ከላይ በተመለከተው ትርጓሜ

መሰረት ማስቀደም የሚገባው ፖለቲካውን መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ፖለቲካውን ነው ሲባልም የሚከተለውን ርዕዮተ አለማዊ ፍልስፍና ለይቶና በግልፅ አስቀምጦ በአላማው ዙሪያ የተሰባሰቡ ሃይሎችን አንቅቶና አደራጅቶ መጀመሪያ ፓርቲውን በሁለት እግሩ ማቆም፣ በመቀጠል ከርዕዮተ አለማዊ ፍልስፍናው የመነጩ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን እንዲሁም የፖለቲካ ፕሮግራሞችን ነድፎና ተንትኖ ለአባላቱና ለህዝቡ ግልፅ ማድረግና ማስተማር፣ ከዚያም በፕሮግራሙ የተስማሙ ሃይሎችን መመልመል፣ ማብቃትና ማንቃት፤ ከእነዚሁ አባላቱም ስለዴሞክራሲ በዴሞክራሲያዊ ምርጫና የአባላት ተሳትፎ የፓርቲውን አመራሮች መምረጥና ይፋ በማድረግ  አባላቱን ከማንቃትና ከማደራጀት ባሻገር ፓርቲውን ሊገነቡ የሚችሉ ስትራቴጂዎችን እየነደፉና ስልቶችንም እየቀመሩ ተወዳዳሪ ወደሚሆኑበት ከፍታ ማሸጋገር ትኩረት ሊሰጡት ይገባ ነበር፡፡

ይህ ደግሞ ዝም ብሎ የሚመጣ ሳይሆን በውስጠ ዴሞክራያዊ አሰራር በውይይትና በክርክር ላይ ተመስርቶ ለብዙሃን ድምፅም በመገዛት ነው፡፡ ከዚያም የሃገሪቱን ተጨባጭና በተለይም በሥልጣን ላይ ካለው መንግሥት ፖሊሲዎች የሚመነጩ ችግሮችን በአግባቡ ተንትኖና ለይቶ አዋጪን የፖሊሲ አማራጭ የተለያዩ ህዝባዊ መድረኮችን ፈጥሮ ምርጫውን ለህዝብ መስጠት ግድ ይላል፡፡ እንዲህ እንዲህ እያሉም ከቀጠሉ በኋላ ተመሳሳይ ርዕዮተ አለማዊ ፍልስፍናን ከሚከተሉና በእርግጥም የትኞቹም በህዝብ ስም ይንቀሳቀሳሉና ስለህዝብ ከቆሙት እውነተኞቹ ጋር በጋራ መስራትና በሂደትም ግንባር እስከመፍጠርና መዋሃድ ለመዝለቅ መስራት ያስፈልጋል፡፡ ከዚያም ብቁ ተወዳዳሪ መሆናቸውን ሲያረጋግጡ፤  አማራጭ ፖሊሲያቸውን እና ፕሮግራማቸውን ይፋ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

ከዚያ ውጪ የሆነው ፕሮፖጋንዳውን  ባልተሰራ ፖለቲካ ውስጥ ቆመው መልቀቅና የገነውን ፓርቲ ስህተቶች እግር በእግር እየተከተሉ መጮህ በምርጫ ፖለቲካ ውስጥ ወሳኝ ለሆነው እና ሁሉም መሰረታችን ነው ለሚሉት ህዝብ አንዳች ነገር የማይፈይድና ይልቁንም ጎጂ የሚሆንበት ዕድል የሰፋ ሊሆን እንደሚችል ከምርጫ 97 ያየነውና ያረጋገጥነው እውነት ነው፡፡  አሳሳቢው ደግሞ ይኸውና ፖለቲካውን ከፕሮፖጋንዳ ያለየው መንገድና መንገደኞች ከዚያኛውና ከምርጫ 97ቱ በከፋ ሁኔታ እየነጎዱበት መሆኑ ነው፡፡

መድረኩን በሁለት እግሩ ማቆም እንደተሳናቸው እያየንም 33ቱ በሚል ጥምረት መፍጨርጨራቸውንም እንደተጠበቀው ከፕሮፖጋንዳ የዘለለ ትርፍ አለማስገኘቱን፣ በመርህ

ይከበር የተጀመረውም መበታተን ሰማያዊ ፓርቲን እንደፈጠረና የአንድነት ሊቀመንበርን አታክቶ ውሳኔ እስከማሳጣት መድረሱን እያየን ነው፡፡ በግርግር የተፈጠረውን እና አስቀድሞም ስልትንና ስትራቴጂን ለይቶ ባላገናዘበ መንገድ የተቋቋመውን መድረክ የተቀላቀሉ ጉምቱ ፖለቲከኞች ከፊሎቹ በበቃኝ፣ ገሚሶቹም በዝምታ የሚበዙት ደግሞ በጋዜጣ ላይ መዘላለፍና መበታተናቸውን እያየን፣ ሰሞንኛ የሆነ እና ስለ ምርጫ 2007 ግቡን የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ያደረገ ውህደት ሰማን፡፡ ይህና በመኢአድና በአንድነት ፓርቲ መካከል ከሰሞኑ ስምምነት ላይ የተደረሰበት ቅድመ ውህደት ግቡ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ነው የምንለውም ፖለቲካውን ሰርተው ሳይጨርሱ በፕሮፖጋንዳ እየጋለቡ በመሆኑ ነው፡፡ ይህ አይነቱ አካሄድም የትም የማያደርስና ይልቁንም ከቀድሞው በከፋ ሁኔታ ፍርክስክሱ የሚወጣ መሆኑ ላይ ጠርጥረን ሳንጨርስ ፍንጮች ማየት መጀመራችንም፣ በእርግጥም ፖለቲካውን እና ፕሮፖጋንዳውን ያለየ የተቃውሞ ፖለቲካ ጉዞ ሩቅ አሳቢ ቅርብ አዳሪነትን እንደሚያስከትል የሚረጋግጥልን ሆኗል፡፡

ከላይ በተመለከተው አግባብ ያልተሰራው የተቃውሞ ፖለቲካ ሁሌም እያሰማን ያለው ፕሮፖጋንዳ ቢያንስ እንኳን ከላይ በተመለከተው አግባብ እንደፕሮፖጋንዳም ንድፈ ሀሳባዊ ትንታኔ ያልተቃኘ እና ጥላቻና ዘለፋን መሰረት ያደረገ መሆኑ እሙን ነው፡፡ ለዚህም በርከት ያሉ ማሳያዎች ቢኖሩም ዋናው ግን ያለመሰረት የተሰራ ቤት መፍረሱ አይቀሬ እንደሆነው ሁሉ ያልዘሩትን ለማጨድ የሚሹቱ ሃይሎች ሁሉ እራሳቸውን በመፈተሽ ለመስተካከልና ለመታረም ከመፍቀድ ይልቅ ግባቸው የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ነውና ሁሉን ነገር ገዢው ስርዓት ላይ ማላከክና ከፍ ሲልም እራሳቸው የሆኑትን እና የደረሰባቸውን መጠላለፍ ለገዢው ስርዓት ማላበስ ዋነኛ መገለጫቸው እየሆነ ነው፡፡

እንግዲህ የሰሞኑ ውህደትና ተጣማሪዎቹ መኢአድ እና አንድነት ፓርቲዎች የተፈራረሙትም በቅድመ ውህደት ደረጃ ላይ መሆኑ ይታወቃል፡፡ እንደጠረጠርነው ደግሞ ወደጋራ ቤታቸው ከመግባታችን በፊት ወደየግል ጓዳቸው ስናማትር በቅድመ ውህደት ማግስት ፖለቲካውን ከፕሮፖጋንዳ ያለየ ገመናቸው እየተጋለጠ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ ከመኢአድ ጓዳ የተገኘው እና ከታች የምናየው ገመና ከሰሞኑ የወጣና ፓርቲውን እንኳንስ ለውህደት በሁለት እግሩ ስለመቆሙ የሚያጠራጥር በዋናነት ደግሞ ፖለቲካውን ከፕሮፖጋንዳ ያለየ ሴራውን የሚያጋልጥ ሁነት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

ይህን ገመና የሚገልጡት ደግሞ የነዚሁ ሃይሎች የፕሮፖጋንዳ ሰለባ የሆነው ገዢው ፓርቲ ወይም ሌላ ሳይሆን እራሳቸውና ስለውህደትና ጥምረት ተናግረው የማይጠግቡ እንደሆኑ የምናውቃቸው የተቃውሞው ፖለቲካ ጉምቱ ሰዎች ናቸው፡፡ (ምንም እንኳን በዚህ ደረጃ ላይ በሚገኝ አዘቅት ውስጥ እንደሆኑ አምነውም  ከገዢው ስርዓት ትከሻ ላይ ያልወረዱ ቢሆንም) የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት- መኢአድን የተመለከተው የጓዳ ገመና የፓርቲው ሊቀመንበር በጠቅላላ ጉባኤ የተመረጡትን የፓርቲውን ከፍተኛ አመራሮች ማሰናበታቸውን የቀጠሉበት መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡ የፓርቲውን የቀድሞ የድርጅት ጉዳይና የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ የነበሩ ከፍተኛ አመራሮች ዋቢ ያደረጉት የመኢአድ ገመናዎች የዚህና ከአንድነት ጋር ቅድመ ውህደት አድርገናል ባሉበት በዚሁ ሳምንት ውስጥ የፓርቲው ፕሬዝዳንት የስራ አስፈፃሚውን መበተናቸው ብቻ ሳይሆን የምክር ቤት አባል ያልሆኑ ሰዎችን ከጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔና ከምርጫ ቦርድ እውቅና ውጪ መሾማቸው ነው፡፡ የዚህ ገመና ዋቢዎች ለዜና ምንጮች እንደተናገሩት ለምክትል ፕሬዝዳንትነት በፕሬዝዳንቱ የግል ፍላጎት የታጨት ግለሰብ ከቄስ ትምህርት በዘለለ መደበኛ ትምህርት ያልቀሰሙ እና በሌጣ ወረቀትም ላይ ሆሄያትን ማስፈር የማይችሉ እንደሆኑና ይህም ቀደም ተብሎ የተጀመረ ፖለቲካዊ ሴራ እንደሆነ ነው፡፡

እነዚህና በፕሬዝዳንቱ የተሰናበቱ አመራሮች እንዳሉት ከሆነም አዲሱ ስራ አስፈፃሚ በውህደቱ ዋዜማ መሾም በራሱ መኢአድ ያልጨረሰው የውስጥ  ትግል ውስጥ እንዳለ ማሳያ እንደሆንና በዲሲፕሊን ስማቸው በበጎ የማይነሱ፤  የትምህርት ደረጃቸው የደከመ ኢትዮጵያ ስላለችበት ነባራዊ ሁኔታና እውነታ ላይ መሰረት አድርገው ፖለቲካዊ ትንታኔ መስጠት የማይችሉ ግለሰቦች በፕሬዝዳንቱ ዙሪያ መኮልኮላቸው ለፓርቲው ጤና እንዳልሆነም የገለፁ ሲሆን፤ እኛ ደግሞ በመግቢያዬ አካባቢ እንደጠቋቆምኩት ያልተሰራውን ፖለቲካ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤትን ግቡ ካደረገው ዓላማ ጋር ለማጣጣም ፖለቲካውን የማያውቁ እና ያልተገነዘቡትን ወደ ስልጣን ማምጣት አማራጩ መንገድ ሆኖ ሊሆን እንደሚችል ጥርጣሬያችንን አስቀምጠን በእርግጥም ፖለቲካውን ከፕሮፖጋዳ ያለየውን የመኢአድ ጉዞ የሚያረጋግጥ እውነት እንመልከት፡፡

ይህና ከላይ የተመለከተው የመኢአድ ገመና በየዜና አውታሩ እየተነገረ እና እየተነበበ ባለበት ሁኔታ ጉዳዩን በተመለከተ በስልጣነ መንበር ላይ ያሉት የፓርቲው አመራሮች አንዲት ነገር ሳይተነፍሱና ሳያስተባብሉ (በእርግጥ የማይሸሹት እውነት በመሆኑ

ተቀብለውታል ብለን ብናምንም) ይህን የመሰለ ፖለቲካ ትተው፤ መኢአድ በምርጫ 2007 ገጠር ድረስ ባለው መዋቅሩ ጠንካራ ተፎካካሪ እንደሆነ በመገመት ገዢው ፓርቲ አባላቴ ላይ የአካልና የህይወት  አደጋ እያደረሰብን ቢሆንም ትግላችን ይቀጥላል›› የሚሉ ፕሮፖጋንዳዎችን የወቅቱ ወይም ጠቅላላ ጉባኤው የማያውቃቸው የመኢአድ ህዝብ ግንኙነት ኃላፊ እየነዙ ይገኛሉ፡፡ ቤታቸው እየፈራረሰ መሆኑን እየሰማን በሰው ደጃፍ ምን አይነት ትግል እንደሚያካሂዱ ግልፅ ባይሆንም ነገርዬውና ምንጩ ፖለቲካን እና ፕሮፖጋንዳን ያለየና የከሸፈ ስትራቴጂው መሆኑ ነው፡፡ የራሷ አሮባት የሰው እንደምታማስለው፤ የራሷ ጓዳ እየተናደባት ከሌላው ጋር ለመጣመር ቢያንስ በተባረሩ ሰዎች ምትክ መተካት አማራጭ ቢመስልም የትም እንደማያደርስና ምናልባትም ያኛውም ተመሳሳይ መሆኑ ዳግም የውድቀቱን ጉዞ ቢያፋጥነው እንጂ ግብ የተደረገው ም/ቤት የመግባት ህልም ውሃ እንደሚበላው ከወዲሁ መገመት አይከብድም፡፡

እነዚህን እና ተዋሃድን የሚሉትን መኢአድና አንድነት የተሰኙ ፓርቲዎች በሌላ መነፅር እንመልከታቸው፡፡ መነፅራችንን የተዋስነው ደግሞ ለወትሮው ስለእነዚህ ፓርቲዎች ሲያራግቡና ቅባቅዱስ ሲቀቡ የነበሩትና በዘረኛ ፖለቲካ አስተሳሰባቸው ከቀደሙት ሚኒሊክ፣ አስኳልና ሌሎች ጋዜጦች ጀምሮ እስከ ፍትህና ፋክት መፅሄቶች ድረስ የምናውቀው ታዲዮስ ታንቱ ነው፡፡ ይህና ከአቶ ታዲዮስ ታንቱ የተዋስነው መነፅርም ልክ እደሌሎቹም አንድ አይናማ ነው፡፡ ምክንያቱ ደግሞ የቀቧቸውን ቅባ ቅዱስ ለማርከስ የሄዱበት መንገድ በገዢው ፓርቲ ላይ የተንጠለጠለ እና ከፖለቲካዊ ትንታኔ ይልቅ አመፃን፣ ተራ ፕሮፖጋንዳንና የፀረዴሞክራሲያዊነት መንገድን የተከተለ በመሆኑ ነው፡፡

አቶ ታዲዮስ ታንቱ ለኢትዮ ምህዳር ጋዜጣ ቅፅ 2 ቁትር 73 ላይ የመኢአድን እና አንድነትን ቅድመ ውህደት ምን ሲሉ ሰየሙት መሰላችሁ፡፡ ‹‹ውህደት የአንጀራ ብልሃት›› በማለት፡፡ ከዚያም በዚህ ስያሜያቸው ስር ካሰፈሩት ዋና ዋናዎቹን ደግሞ እንመልከት፡፡ ‹‹ለህዝብ የማይጨነቁ›› የሃገር ጉዳይ የማያንገበግባቸው፣ የንድፈ ሃሳብ እወቀት የሌላቸው፣ ለህወሃት በዓመታት አገልግለው ጡረታቸውን ያስከበሩ›› በማለት ቅድመ ውህደት የተፈራረሙትን ፓርቲዎችና አመራሮች ገመና የሚገልጡት አቶ ታዲዮስ ‹‹የሚሄዱበትና የሚያደርጉት ጠፍቷቸው በስነመንግስት ማህበራት ስር የተጠለሉ፣ የማደራጀት ብቃት የጎደላቸው፣ በህወሃት መመሪያ የሚንቀሳቀሱ፣ እንኳንስ ህዝብን እንደዕብራዊው ሙሴ ነፃ ሊያወጡ ቀርቶ ራሳቸው በህሊናቸው ተገዢነትን በፀጋ የተቀበሉ፣ ሁለት የሥነመንግስት

ማህበራት ውህደት ቢፈራረሙ ምን ውጤት ሊኖር ይችላል?›› በማለትም ማንን እንደሆነ ለመገመት ያዳገተ ጥያቄ ያነሳሉ፡፡

ጥያቄው ለእርሳቸውና ለራሳቸው መሆኑን የሚያጠራጥር ሃሳብ ግን አልጠፋም፤ ምክንያቱም ወረድ ብለው ‹‹ፎርማ የእንጀራ ፈላጊዎች ጨዋታ ነው›› ሲሉ መልሰዋልና፡፡ እኔን የገረመኝ እስከዛሬ ቅባ ቅዱስ ሲቀቧቸው የነበሩት እነዚህ ፓርቲዎች ዛሬ ላይ ነው የተገለጡላቸው? የሚለውን ጥያቄ ስናነሳ የሚገኘው ምላሽ ነው፡፡ ይኸውም አይደለም እነርሱ እራሳቸው ፕሮፓጋንዳውን ከፖለቲካው ያለየ አካሄድ ሰለባ በመሆናቸው ነው፡፡ ወይም ደግሞ ምናልባት የፓርቲዎቹና የአመራሮቹ ገመና እርሳቸው እንዳሉት እውነትም ከሆነ እውነታውን መተቸትና ዴሞክራሲያዊ መንገዱን ማመላከት ሲገባ በማንኳሰስ የተመኙት አመፅ እንዳይከሽፍ በመስጋታቸው ነው፡፡ ሁለተኛው የቢሆን ምላሻችን ግን ትክክል ይመስላል፡፡ ለምን ቢሉ አቶ ታዲዎስ የቅድመ ውህደቱን ስምምነት ‹‹ፎርማ ግን ባዶ የሰነድ ጨዋታ ነው፣ ፎርማ የፈሪዎችና የወላዋዮች የማስመሰያ የስነመንግስት ጨዋታ ነው። ፎርማ የቀድሞ የኢህአፓ ጀሌዎች የህወሃት ትርፍራፊዎችና ከወህኒ ቤት ይቅርታ ጠይቀው የወጡ የቅንጅት አልቃሾች ስሜት ማርኪያ ባዶ ጩኸት ነው።›› ሲሉ ገልፀውታልና፡፡

በእርግጥ ለመድብለ ፓርቲ ዴሞክራያዊ ስርዓት ግንባታ ተብሎ የሚደረግና ፖለቲካን ያስቀደመ ውህደት የሚደገፍና ሊበረታታ የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡ ያም ሆኖ ግን የእነዚህ ውህደት ፖለቲካን የገፋና ፕሮፓጋንዳን ያስቀደመ በመሆኑ አቶ ታዲዎስ እንዳሉትም የቅንጅት አልቃሾች ጨዋታ ቢሆንም ህወሃትን ከኢህአፓ ጋር ያገናኙበት አግባብ ግን ስሜታዊነታቸውን እና እየጠፉ ናቸው የሚሏቸውን ወላዋዮችና አልቃሾችም እንኳ ቢሆን ለመተቸት አቅሙና ብቃቱ የሌላቸው መሆኑን የሚያረጋግጥና የባሰው አዘቅት ውስጥ ያሉትም እርሳቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡

የቅድመ ውህደት ስምምነት ፎርማ ያኖሩትን መኢአድና አንድነት ራሱን ማእከል አድርጎ የሚንቀሳቀስ ማህበር በመሆኑ የዘገየ ቢመስልም ህዝባዊ መሰረት ስለሌለው ፍፃሜው በውድቀት ይጠናቀቃል ቢሉምና እኛም የምንስማማበት ቢሆንም አንድ አመት ከስምንት ወር መታሰርን እና ይቅርታ መጠየቅን ከመንፈሰ ልልነትና ከነፃ አውጭነት አንፃር ጋር ማያያዛቸውን ግን ፖለቲካዊ ሳይሆን የረከሰ ፕሮፓጋንዳዊ ምልክት ነው ብለን እንድንወስድባቸው እንገደዳለን፡፡

በሌላም በኩል‹‹በሃገር ስም ድብቅ ዓላማን ለማሳካት መነሳት ፍፃሜው ምን ሊሆን እንደሚችል ይታወቃል፡፡ ዝናና ገንዘብ ለማግኘት መንቀሳቀስ በምንም መለኪያ የነፃነት ትግል ተደርጎ ሊወሰድ አይችልም፡፡›› የሚለውን ውህደቱን የተመለከተ ገመና ግን ብናነሳ ከላይ በተመለከቱ የፖለቲካና የፕሮፖጋንዳ ንድፊ ሀሳባዊ የተጠየቅ አመንክዮ ትክክል እንሆናለን፡፡ ፖለቲካውን ከፕሮፖጋንዳው በኋላ ያደረገ የተቃውሞ ፖለቲካ ሂደት ግቡም የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት መሆኑን በተጨባጭ የሚያረጋግጡ ሁለት መነፅሮችን ደግሞ ከ33ቱ ወደ አስራዎቹ በወረዱትና ምንም መፈየድ ያልቻሉት ተጣማሪዎች ሊቀመንበርና፤ ባደረባቸው የኪራይ ሰብሳቢነት በሽታ ተለክፈው ከገዢው ፓርቲ ወደ ተቃዋሚዎቹ መንደር ከዘለቁት የቀድሞው የህወሃት ግንባር ቀደም ታጋይ ተውሰን በክፍል ሁለት የምናየው ስለሆነ ጉዳያችንን ለዛሬው በዚህ እንቋጭ፡፡